የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት
Refugees and Returnees Service

UNHCR
The UN Refugee Agency

PRESS RELEASE

**ቦታ**
አዲስ አበባ

**ቀን**
ሐሙስ ሚያዝያ
3 /2016

# በኢትዮጵያ ወደ 1 ሚሊዮን የሚጠጉ ስደተኞች በገንዘብ ድጋፍ እጥረት ምክንያት ለከፋችግር ይጋለጣሉ ሲሉ የተመድ የስደተኞች ኤጀንሲ (UNHCR)፣ የኢፌዴሪ የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት (RRS) እና አጋሮች አስጠንቅቀዋል።

**[ኢትዮጵያ]** *እ.ኤ.አ. መጋቢት 20 ቀን የኢትዮጵያ መንግሥት የስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት (RRS)፣ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኤጀንሲ (UNHCR) እና ከ130 በላይ አጋሮች፣ የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች፣ የመንግስት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች፣ ሀገር አቀፍ እና ዓለምአቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ስደተኞች እና የግሉ ሴክተር ተሰባስበው፣ ከአሁን በፊት ታይቶ በማይታወቅ መልኩ የገንዘብ ድጋፍ ችግር መከሰቱ በሀገሪቱ ውስጥ ለሚኖሩ 1 ሚሊዮን የሚሆኑ ስደተኞች የሚሰጠውን እርዳታ አደጋ ላይ ይጥላል ሲሉ አሳስበዋል።*

"በአብሮነት ከስደተኞች ጋር" በሚል ርዕስ በተካሄደው በዚሁ የአጋር አካላት ጉባዔ፣ የሰብዓዊ እና ልማት አጋሮች፣ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ምላሽ ለመስጠት ይቻል ዘንድ ለጋሾች ተጨማሪ ድጋፍ እንዲያደርጉ አሳስበዋል። ውይይቱም ገና ይፋ ላልተደረገው የያዝነው ዓመት የስደተኞች ምላሽ ዕቅድ ዝግጅት በር ከፋች ነው።

የስደተተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ጠይባ ሀሰን የተፈጠረው የድጋፍ እጥረት በስደተኞች ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ አሳሳቢ መሆኑን ሲገልጹ "ስደተኞች በድጋፍ እጥረት ምክንያት የከፋ ተፅዕኖ ውስጥ ሲወድቁ መመልከት በጣም ያሳዝናል፤ ለዚህም ዋናው ምክንያት ለአጠቃላይ የስደተኛ ምላሽ የሚያስፈልገው የድጋፍ መጠን ማሰባሰብ ከተቻለው ኃብት በእጅጉ የላቀ መሆኑ ነው።" ብለዋል። አክለውም "መንግሥት የገባቸውን ቃልኪዳኖች በቁርጠኝነት እንዲፈጽምና ስደተኞችንና ጥገኝነት ጠያቂዎችን የማስተናገድ የተለመደ ኃላፊነቱን መወጣቱን እንዲቀጥል ለማስቻል የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ድጋፍ ወሳኝ ነው።" ሲሉ ገልጸዋል።

የድጋፍ መመናመኑ ከፍተኛ ተጽዕኖ ካሳደረባቸው ዋና ዋና ዘርፎች ትምህርት አንዱ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ለትምህርት ከደረሱ ስደተኛ ህፃናት ወደ ትምህርት ቤት መሄድ የቻሉት ግማሽ ያህሉ ብቻ ናቸው። የመማሪያ ክፍሎች መጨናነቅ እና እስከ 80 በመቶ የሚደርሱ ህጻናት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ማቋረጣቸው ችግሩን ተደራራቢ ያደርገዋል። ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ካልተገኘ፣ አብዛኛውን የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ መምህራንን ደመወዝ መክፈል አይቻልም፤ ይህም በአገሪቱ በ23 የስደተኞች ማዕከላት የሚገኙ ትምህርት ቤቶች እንዲዘጉ ያደርጋል።

የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት
Refugees and Returnees Service

UNHCR
The UN Refugee Agency

**ቦታ**
አዲስ አበባ

**ቀን**
ሐሙስ ሚያዝያ 3 /2016

**ርእስ**
በኢትዮጵያ ወደ 1 ሚሊዮን የሚጠጉ ስደተኞች ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ የገንዘብ ድጋፍ እጥረት ምክንያት ለከፋ ችግር ይጋለጣሉ ሲሉ የተመድ የስደተኞች ኤጀንሲ (UNHCR)፣ የኢፌዴሪ የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት (RRS) እና አጋሮች አስጠንቅቀዋል።

አስፈላጊ የሆኑ መድሃኒቶችና የህክምና መሣሪያዎች እጥረት የአጋር አካላትን በሽታዎችን የመከላከልና ምላሽ የመስጠት አቅም አዳክሟል። በዚህም ምክንያት በያዝነው ዓመት መከላከል ይቻል የነበረ በ2023 ካጋጠመው በእጥፍ የስደተኞች ሞት ሊከሰት ይችላል።

"የገንዘብ እጥረቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ የስደተኞችን እና በልግስና የሚያስተናግዷቸውን ማህበረሰቦች ህይወት ወደ ከፋ ሁኔታ እያስገባ መምጣቱ ግልጽ ነው።" ሲሉ በኢትዮጵያ የተመድ የስደተኞች ኤጀንሲ ተወካይ፣ አንድሪው ምቦጎሪ ተናግረዋል። "በአጋርነትና በትብብር መንፈስ አብረን ለመስራት ያለን ቁርጠኝነት የማይናወጥ ነው። ነገር ግን አስተማማኝ የገንዘብ ድጋፍ ከሌለ የተመድ የስደተኞች ኤጀንሲ፣ የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት እና አጋሮች ለስደተኞች የህይወት አድን እርዳታ መስጠት አይችሉም፤ ስደተኞችና አስተናጋጅ ማህበረሰቦች መሠረታዊ አገልግሎቶችን እና ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድሎችን የሚያገኙበትን ሁኔታ ማረጋገጥም የማይቻል ይሆናል።" ሲሉ ምቦጎሪ ጨምረዋል።

"አሁን እርምጃ የምንወስድበት ጊዜ ነው። ችግሮቹን አውቀናል፤ ከመንግሥት እና ከሲቪል ማህበረሰቡ ጋር ጠንካራ አጋርነት አለን፤ እናም ዘላቂ መፍትሄዎችን ለማግኘት ቆርጠን ተነስተናል። ነገር ግን ድጋፍ ከሌለ ብዙ መሥራት አንችልም።" በማለት የተመድ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ ዕርዳታ አስተባባሪ፣ ዶክተር ራሚዝ አላክባሮቭ ተናግረዋል።

በተጨማሪም፣ ስደተኞች ራሳቸው በጤና፣ በትምህርት እና በውሃ አቅርቦት ላይ ያሉ ክፍተቶች በቀጥታ በሕይወታቸው ላይ ጫና እያሳደሩ እንደሆነ ሀሳብ አካፍለዋል።

"መምህራን በቂ ደሞዝ ስለሌላቸው ሁልጊዜ በትምህርት ቤት በመገኘት ትምህርት አይሰጡም፤ በዚህም የተነሳ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ይተውና ሌሎች አሉታዊ ተግባራትን ያከናውናሉ።" ሲል በጋምቤላ ከተማ ተማሪ የሆነው የ23 ዓመት ወጣት፣ ጋትቼው ተናግሯል።

"እዚህ ያለው ሆስፒታል መድኃኒት የለውም፤ ስለዚህ መድኃኒት ለማግኘት ሩቅ መንገድ ለመጓዝ ምግባችንን ሸጠን ከፍተኛ የትራንስፖርት ክፍያ መክፈል አለብን።" ስትል በሚርቃን ስደተኞች ዕከል የምትኖር ሶማሊያዊት ስደተኛ፣ ሂንዳ ተናግራለች።

በቂ የገንዘብ ድጋፍ አለመገኘቱ በሱዳን የተከሰተውን ግጭት ሸሽተው ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ ያሉ ሰዎች ንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዳያገኙ እያደረገ በመሆኑ ለበሽታ ይጋለጣሉ።

"በጣቢያው ላይ የንጹህ ውሃ እጥረት ስላለ ብዙ ጊዜ በጣም ሩቅ ከሆነው ወንዝ የቆሸሸ ውሃ ማምጣት ይኖርብናል። ውሃው ለመጠጥ ምቹ ባለመሆኑ ህጻናት እንደ ተቅማጥ ባሉ ብዙ የጤና እክሎች እየተሰቃዩ ነው።" ስትል በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በኩርሙክ የሽግግር ጣቢያ ውስጥ የምትገኝ ሱዳናዊት ስደተኛ፣ ሩፋፊዳህ ተናግራለች።

ኢትዮጵያ ከ1 ሚሊዮን በላይ ስደተኞችን እና ጥገኝነት ጠያቂዎችን በማስተናገድ ላይ የምትገኝ ሲሆን ከአፍሪካ ሶስተኛዋ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ስደተኛ አስተናጋጅ ሀገር ነች። በሱዳን ያለውን ግጭት ሸሽተው ከ50,000 የሚበልጡ ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ከለላ አግኝተዋል። የስደተኞችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል፣ ብሔራዊ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የሚያስችል መዋዕለ ንዋይ ፈሰስ ለማድረግ፣

**ቦታ**
አዲስ አበባ

**ቀን**
ሐሙስ ሚያዝያ 3 /2016

**ርእስ**
በኢትዮጵያ ወደ 1 ሚሊዮን የሚጠጉ ስደተኞች ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ የገንዘብ ድጋፍ እጥረት ምክንያት ለከፋ ችግር ይጋለጣሉ ሲሉ የተመድ የስደተኞች ኤጀንሲ (UNHCR)፣ የኢፌዴሪ የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት (RRS) እና አጋሮች አስጠንቅቀዋል።

የማህበረሰብን ችግር የመቋቋም አቅም ለማሳደግ እንዲሁም ከተቀባይ ማህበረሰብ ጋር በሰላም አብሮ የመኖር ሁኔታን ለማሻሻል የለጋሾች ድጋፍ እንደሚያስፈለግ የተመድ የስደተኞች ኤጀንሲ ገልጿል።

ለበለጠ መረጃ የሚቀጥሉትን ሰዎች ያነጋግሩ:

- በአዲስ አበባ፣ **በአካል ንጉሴ** ፡ beakaln@rrs.gov.et,+251 94 410 0053
- በአዲስ አበባ, **Lucrezia Vittori**, vittori@unhcr.org, + 251 97 810 4031
- በናይሮቢ (regional), **Faith Kasina**, kasina@unhcr.org, +254 113 427 094